# በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን የኢህአዴግ አጋር መድረክ የድጋፍ መግለጫ

በሐዋሳ ከተማ በተካሄደው የኢህአዴግ ሰባተኛ ድርጅታዊ ጉባኤ ላይ በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን የኢህአዴግ አጋር መድረክ /EPRDF SUPPORT FORUM/ የቀረበ የድጋፍ መግለጫ

መስከረም 6፤ 2001 ዓ/ም

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትርና የኢህአዴግ ሊቀመንበር አቶ መለስ ዜናዊ እንዲሁም የተከበራችሁ የኢህአዴግ 7ኛ ድርጅታዊ ጉባኤ ተሳታፊዎች በዛሬው ዕለት በሰሜን አሜሪካ፣ በካናዳ፣ በአውሮፓና በአውስትራሊያ የሚገኙ ኢትዮጵያኖች የመሰረቱትን የኢህአዴግ አጋር መድረክ /EPRDF SUPPORT FORUM/ ወክዬ በአባሎቹ በቦርዱ እንዲሁም በሊቀመንበራችን በአቶ መኮንን ካሳ ስም ሆኘ ይህንን መግለጫ እሰጣለሁ።

መስከረም አምስት 2001 ላይ በሚካሄደው የሰባተኛ ኢህአዴግ ጉባኤ ላይ ተካፋይ እንድንሆን ለቀረበልን ጥሪ ወሰን የለሽ ደስታችንን አስቀድመን እንገልፃለን። ኢህኤዴግ ይህንን ጥሪ ስያደርግልን ያነሳሳንን ዓላማና በስራ እንድንፈጽመው አቅደን በመስራት ላይ ያለነውን ቁምነገር ይዘትና እምነት በመንተራስ እንደሆነ ጥርጥር የለንም።

የኢህአዴግ ዓላማና አባይት ክንውኖች የኢትዮጵያ ህዝቦችን ለዘመናት ተጠናውቶ እንቅፋት ከሆናቸው የፖለቲካ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ኋላ ቀርነት ለማላቀቅ የሚደረጉ የረጅምና የአጭር ጊዜ ተከታታይ ስራዎች መሆናቸውን አጥብቀን እንገነዘባለን። ስለዚህም ጥሪውን በደስታ በመቀበል ብቻ ሳይሆን በተግባርም ደጋፊና አቃፊ እጆች እንደሆንም በማያወላዳ መንገድ ደግመን ለመግለጽ እንወዳለን።

የተከበራችሁ የኢህአዴግ የሰባተኛው ጉባኤ ተሳታፊዎች የኢህአዴግን መሠረታዊ መፈክሮች ደግፈን አብረን በህብረት ለመስራት ያነሳሱን ምክንያቶች በዛና ላቅ ያሉ ቢሆኑም አበይቶቹን ለመጥቀስ እንወዳለን። አብዮታዊ ዴሞክራሲን መሠረት በማድረግ የኢትዮጵያ መላ ህዝቦች በእኩልነት ወደ ተጠናከረ አንድነት ይመጡ ዘንድ ብሔርና ብሔረሰቦች ራሳቸውን በራሳቸው አስተዳድረው ቋንቋና ሌሎችም ጠቃሚ ወግና ባህሎችን ጠብቀውና አጎልብተው ከዛሬ ነገ የኑሮ ደረጃቸው ከፍ ይል ዘንድ ኢህአዴግ አመርቂና ያልተቆጠበ ስራ በመስራት ላይ ይገኛል።

ይህ ስራ ዴሞክራሲን ከማጎልበት ጋራ በእጅጉ የተያያዘ እንደሆነ አያጠያይቅም። እንደኛ እምነት አብይ የሰው ልጆች መብት ተገላጭነት የሚያገኘው የህዝቦችንና የአንድን ህዝብ የጋራ መብት ያለምንም ፍራቻና ጥርጣሬ በማክበር ላይ ሲመሰረት ብቻ ነው እንላለን። በትረ መንግስቱን ከሐይማኖት ነፃ በማድረግ የህዝቦችንና የግለሰቦችን የእምነት መብት እንዲከበር፣ ኋላ ቀር የሆኑ ወጋዊ አስተሳሰቦችና ተግባሮች ለአንዴም ለሁሌም ተወግደው የፆታ እኩልነት ሊታይና ሊጨበጥ በሚችል መንገድ፣ ንብረት አልባ ባለንብረት፣ የመንግስት ተቋሞችን ግልጋሎት ያለ አድልኦ ያገኙ ዘንድ፣ በፍራቻ በምን ይሉኛል ባይነት ሳይገታ የሐሳብ ፍንዳታ እንደ አሸን ይከሰት ዘንድ፣ በርካታ መድረኮችንና ተቋሞችን በመመስረት ሰላማዊ ጉርብትናን በመሻት ከወታደራዊ ጉልበት ይልቅ ድርድርንና መቻቻልን መርጦ የህዝባችንን የአገራችንን ህልውና ለሚጋፉት ደግሞ የማያደግም ጠንካራ ህዝባዊ ክንድ በመሰንዘር ኢህአዴግ ላደረጋቸው ኢትዮጵያዊ ተጋድሎዎች ሁሉ ሊመሰገንና ሊታገዝ የሚገባው ተግባር ለመሆኑ ምስክሮች ነን።

የኢህአዴግ አጋር መድረክ ይህንን የኢህአዴግ ዓላማ የሚፃረር ጎጂ ህግ በአሜሪካ ውስጥ እንዳይረቅ በመታገል፣ የህዝባችንና የአገራችን ስም በሐሰት ዜናና በጎጂ ቅስቀሳ እንዳይጎድፍ በመቋቋም፣ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን በልማት ስራ እንዲሳተፉ በማበረታታት የምግብ እጥረትን ለመቅረፍ የሚረዳ ገንዘባዊ መዋጮ በመሰብሰብ አስተዋጽኦ አድርገናል እያደረግንም ነው።

እናም ጥሪውን ስንቀበል በእምነት ላይ የተመሰረተ ኩራት እየተሰማን የድርጅታችንን ፀሓፊ ወይዘሮ ሻሾ ሐብቱን ሙሉ በሙሉ በጉባኤው ላይ እንዲትሳተፍ ወክለን ሸኝተናታል። እንደ አጋርና ደጋፊ እጆች የምንቆምለት ኢህአዴግም እጁን ዘርግቶ ተቀብሏት የአገራችን ችግሮች በበለጠ እንድንቀርፍ የሚያስችለን ሰፊና ጠለቅ ያለ ግንኙነት አጎልባች ውይይት ላይ ይጋብዛት ዘንድ በተስፋ እንጠብቃለን። መልከም ሰባተኛ ጉባኤ!

ለህዝባችንና ለአገራችን ከኢህአዴግ ጋር በጋራ እንሰራለን፤ እናመሰግናለን።

በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን የኢህአዴግ አጋር መድረክ
/EPRDF Support Forum/